ተጉም ያዘለ ለውጥ ማድረግ

ማርች 8፣ 2016

# ህዝባዊ ት/ቤቶች፡- የChoice እና የልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች

## የግኝቶችና የውሳኔ ሀሳብ ዘገባ

ገቢ የተደረገው ለ
Montgomery County የትምህርት ቦርድ

metis associates

120 Wall Street
21st Floor
New York, New York 10005
212-425-8833
www.metisassociates.com

# አጭር ማጠቃለያ እና የዲስትሪክት-ደረጃ ውጤቶች

## መግቢያ

Montgomery County Public Schools (MCPS) የሃገሪቱ 17ኛው ታላቅ የት/ቤት ስርአት ነው፣ 37 National Blue Ribbon ት/ቤቶችን ጨምሮ፣ በ202 ት/ቤቶች ከ156,000 ተማሪዎች በላይ ተማሪዎችን እያገለገለ። MCPS እከ157 የተለያዩ አገሮች የመጡና 138 የትውልድ ቋንቋዎች ከሚናገሩ ተማሪዎች ጋር ከአገሪቱ ጅጉን አይነተ-ብዙ/diverse የት/ቤት ስርአቶች አንዱ ነው። ስድስት የMCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ*Washington Post* የ2015 High School Challenge/የሁለተኛ ደረጃ ፈተና ከከፍተኞቹ 200 መካከል ሆነው፤ እናም በሃገሪቱ ከሚገኙት የሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 11% ብቻ ከሚያካትተው ሁሉም 25ቱ የMCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዝርዝሩ ውስጥ ታይተዋል። በ2010፣ MCPS፣ ለአፈፃፀም ልቀት ለአሜሪካዊ ድርጅቶች የሚሰጠው፣ እጅግ ከፍተኛ ፕሬዚደንታዊ ክብር፣ የMalcolm Baldrige National Quality Award/ማልኮም ሪጅ ብሄራዊ ሽልማት ተቀባይ ነበር።

MCPS ተማሪዎችን የተለያየ ምርጫ እና ከአካባቢያቸው የክትትል ውጭ በሆኑ ት/ቤቶች ልዩ ትምህርት ለመቀበል እድሎች ለመስጠት የተተለሙ ሌሎች ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች የማቅረብ ረጅም ታሪክ አለው። እነዚህ ፕሮግራሞች ሙሉና ከፊል የቋንቋ ዝፍቀት/immersion ፕሮግራሞች በኤሌሜንታሪና መካከለኛ ት/ቤቶች፤ ከፍተኛ ተሰጥኦ ላላቸው ተማሪዎች የኤሌምንታሪ ማእከሎች፤ ምርጥ የመቀበያ መስፈርቶች ያሏቸው የማግኔትና የሌሎች የትግበራ ፕሮግራሞች በመካከለኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃዎች፤ እና ሴማዊ የማስተማር ምርጫዎች የሚያቀርቡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ የአካባቢ ኮንሶርሻ እና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ኮንሶሽም በእጣ-የተመሰረተ የምዝገባ ሂደቶችን ያካትታል። በ2013-2014 ውስጥ፣ MCPS የዲስትርክቱ የተማሪ ህዝብ 14.5% ለሆኑት፣ በግማት ለ22,700 ተማሪዎች ባጠቃላይ ላገለገሉ 36 ት/ቤቶች 43 አማራጭ/choice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች አቅርቧል። በተጨማሪ፣ በግምት 8,000 ሌሎች ተማሪዎች (የMCPS ተማሪዎች 5.2%) በመኖሪያቸው መሰረት ከተመደበው የት/ቤት ክልል ውጭ በት/ቤት ምደባ ለውጥ (COSA) አማካይነት ወይም በሌላ አስተዳደራዊ ምክንያቶች ተከታትለዋል።

Montgomery County ከአንድ ሚልዮን በላይ ነዋሪዎች አሉት በህዝብ ብዛትና በአይነተ-ብዙነት/diversityም እያደገ ነው። የዲድትሪክት-ደረጃ ምዝገባ ስርአቱ ባለፉት 20 አመቶች በተማሪዎች ቁጥር እና በአይነተ-ብዙነት/diversity ትርጉም ያዘሉ ጭማሪዎች ተሞክሮ አሳልፏል። የተወሰኑ አካባቢዎች በካውንቲው ደቡባዊ-ምስራቅ ክፋል እና በሜትሮ ሬድ ላይን ያሉትን ጨምሮ ከሌሎች እጅጉን የበለጠ እድገት አይተዋል። MCPS Division of Long-range Planning/የረጅም ጊዜ ፕላን ዝግጅት ክፍል በቀረበ የተማሪዎች ምዝገባ መሰረት፣ የጥቁር/አፍሪካን አሜሪካን፣ ሂስፓኒክ/ላቲኖ፣ እና የባለአነስተኛ ገቢ ተማሪዎች ምዝገባ በተአምራዊ መጠን አድጓል—ባለፉት አስር ዘመኖች እስከ 20 የመቶኛ ነጥቦቸች—በታሪክ የከፍትኛ-ድህነት ት/ቤት በነበሩ ት/ቤቶች ውስጥ። ከዚህም የተነሳ፣ በአሁኑ ወቅት MCPS በካውንቲው ውስጥ በተወሰኑ ት/ቤቶች የመህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ እና የዘር/ትውልድ ቡድኖች ተማሪዎች በማደግ ላይ የሚገኝ ክምችት እያጋጠመው ይገኛል።

በጃንዩወሪ 2015፣ የMontgomery County የትምህርት ቦርድ (Board) ለMetis Associates የተለያዩ ምርጫ/choice እና MCPS የሚያቀርባቸው ሌሎች ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞችን አጠቃላይ ጥናት እንዲያከናውን ውል ሰጠ። ጥናት የተተለመው አራት ዋና ዋና ግቦችን እንዲመለከት ነው፡-

- የያንዳንዱን የMCPS choice እና ሌሎች ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ተወዳዳሪ የሌለው ታሪክ እና ወቅታዊ ይዘት መገንዘብ፤
- የእነዚህን ፕሮግራሞች የየንዳንዳቸውን የተነሱባቸውን አላማዎች መለየትና እነዚህን አላማዎች እያሟሉ እንደሆነ መገምገም፤
- ሁሉም ተማሪዎች ለነዚህ ፕሮግራሞች ርትአዊ መዳረሻ እንዳላቸው መገምገም፣ በተለይም ከቅጣዩ የMCPS ተመሪዎች ምዝገባ እና ከአካባቢው የህዝብ ይዞታ አንፃር፣ በካውንቲ-አቅፍና እና በጎረቤት በሁለቱም ደረጃ፤ እና
- እነዚህ ፕሮግራሞች፣ በተናጠልና አንድላይ በሁለቱ ወገን፣ ተልእኮውን በውጤታማነት ለማራመድ፣ ዋነኛ አላማ፤ ዋነኛ እሴቶች፣ ርትአዊነትን ጨምሮ፤ እና በMCPS Strategic Planning Framework/ስልታዊ የፕላን መዋቅር (SPF) ውስጥ የተቀመጡ ዋነኛ ብቃቶች፣ *የወደፊታችንን አብረን መገንባት፤- ተማሪዎች፤ ሰራተኞች፤ እና ማህበረሰብ* በጥሩ ቦታ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

ምርምሩ በሶስት ምእራፎች እየተካሄደ ነው። ይህ ዘገባ በምእራፍ 1፣ ስለ MCPS choiceና ሌሎች ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ታሪክና ወቅታዊ ሁኔታ አሀዞችና መረጃዎች መሰብሰብና መተንተን የሚያካትት፣ እና በምእራፍ 2፣ በሌሎች ዲስትሪክቶች አዲስ ሀሳብ ፈጣሪዎች፣ ከፍተኛ ጥረት ፕሮግራሞችን መመዝገብ እና ከተማሪዎች የአካባቢ ት/ቤቶች ውጭ ለሚገኙ የትምህርት አማራጮች መዳረሻ ላይ ግምገማና አካዴሚያዊ ምርምርን የሚያካትት፣ የተገኙትን ያቀርባል። ምእራፍ 3፣ ከዚህ ዘገባ አቅርቦት በኋላ ከማርች እስከ ሜይ 2016 የሚካሄደው፣ ለMCPS choiceና ሌሎች ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ከተሳትፎና አስተያየት ከማህበረሰብ ባለጉዳዮች ጋር የትብብሮሽ የትግባሬ ፕላን ማዳበርን ያስከትላል።

## የጥናት ዘዴ

የMCPS choiceና ሌሎች ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ጥናት የአይነትና የብዛት አሀዞች ከበርካታ ምንጮችና የባለጉዳይ ቡድኖች ለመሰብሰብ በድብልቅ-አይነት/mixed-methods አቀራረብ ጥቅም ላይ አዋለ። የአሀዞች አሰባሰብና ትንተና ዘዴዎች የሚከተሉትን ድርጊቶች አካተተ፡-

- **የሰነዳ ድህረ እይታ** ስለMCPS choiceና ሌሎች ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ታሪካዊ ጋዜጣዎች፣ መመርያዎች፣ ዘገባዎች፣ እና ሌላ ሰነድ።

- **መመዘኛ ማርክ ማድረግና ምርምር** ከMCPS ጋር ተመሳሳይ ስፋትና ዴሞግራፊክስ ካላቸው በሌሎች የት/ቤት ዲስትሪክቶች የተተገበሩ የላቁ ልምዶችና ውጤታማ ስልቶችን ለመሰብሰብ።

- **የዲስትሪክትና የማህበረሰብ አስተያየት** በግላዊና በአነስተኛ ቡድን ቃለ መጠይቆች ከ15 ወቅታዊና የቀድሞ የቦርድ አባሎች፣ 36 ሌሎች ወቅታዊና የቀድሞ የማእከላዊ ፅ/ቤት ሰራተኞች፣ 10 የMCPS ወላጅ ማህበረሰብ አስተባባሪዎች፤ እና 32 የማህበረሰብ መሪዎችና የውጭ ባለጉዳዮች የMCPS choice እና ልዩ አክዴሚያዊ ፕሮግራሞች ሰፊ ታሪካዊ እውቅና ያላቸው።
- **የሰፈር ጉብኝት** ከት/ቤት መሪዎች፤ ከ125 መምህራን፣ 354 የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ እና 303 ወላጆች ያሏችው የትኩረት ቡድኖች፤ እና በትምህርት ክፍልና ት/ቤት ግብኝቶች ጋር ግላዊ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ choice እና ልዩ አክዴሚያዊ ፕሮግራሞች ከሚያቀርቡ 36 ት/ቤቶች ውስጥ በ20 ናሙናዎች ተካሂደዋል።

- ***መስመር ላይ የማህበረሰብ ዳሰሳ ጥናቶች*** በመስመር ላይ በተካሄደ ዳሰሳ ጥናት አስደሳች ውጤት የሚወክለው፣ 5,318 መልሶች ያስገኘው ከሴፕተምበር 28 እስከ ኦክቶበር 26፣ 2015 በእንግሊዘኛና በስፓኒሽ ተካሂዷል። በተጨማሪ፣ ከሜይ እስከ ዲሰምበር 2015 ድረስ የመስመር ላይ የአስተያየት ሳጥን ውስጥ በድምሩ 976 አስተያየቶች ተሰጥቷል።

- ***የተማሪ አሀዞች ትንተናዎች።***የሚከተሉትን መስኮች ለመፈተሽ ሰፋ ያለ የተማሪ-ደረጃ አሀዞች ትንተና ተካሂዷል፡- ***የተማሪ ማመልከቻዎች*** ለchoice እና ልዩ አክዴሚያዊ ፕሮግራሞች ፤ ***የተማሪ ምዝገባ*** በፕሮግራሞች እና በዲስትሪክት-አቀፍ፤ ***ኮንሰርሽየም*** ምዝገባዎችና የሎተሪ/እጣ ውጤቶች፤ ***አካዴሚያዊ ግኝት*** የውጤት ምእራፎች፤ ***የት/ቤት ምደባ ለውጥ*** ጥያቄዎችና ፈቃዶች።

- ***የባለሙያዎች ጓድ ድህረ እይታተመራማሪዎች፤*** በትምህርት ርትአዊነትና በchoice፣ በባለተስጥኦ ትምህርት፣ በቋንቋ ማስተማር፣ እና በማግኔት ፕሮግራሞች መስኮች ከምርምሩ የፈለቁ ቁልፍ ግኝቶችና አሀዞች ድህረ እይታ ለማድረግ የባለሙያዎች ጓድ በመለየትና በመሰብሰብ ከMCPS ጋር አብረው ሰርተዋል። የባለሙያ አባለት ጓድ ከጥናቱ የቁሳቁሶች ማጠቃለያ ድህረ እይታ አድርጎ በዲሰምበር 2015 በጥናቱ በቁልፍ ጉዳዮች አስተያየት ግንዛቤና የውሳኔ ሃሳብ ለመስጠት ተሰበሰበ። ከባለሙያ ጓድ አስተያየት የመጨረሻ ዘገባው ላይ ተወሀህዷል።

## *የግኝቶችና የውሳኔ ሀሳቦች ማጠቃለያ*

*ስለ የMCPS choice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ዘገባ ውስጥ ባጠቃላይ የቀረቡት አሀዞችና ውጤቶች በሙሉ የሚያመለክቱት MCPS የእነዚህን ፕሮግራሞች ከዲስትሪክቱ SPF ጋር መቀነባበራቸውን ሲገመግም ወደ ስምንት ሰፋፊ ግኝቶችን ያመለክታሉ። እያንዳንዱ ግኝት MCPSን በchoice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች አማካይነት የተሻለ የመዳረሻ ርትእዊነት እና ልቀት ለማግኘት የሚያግዙ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ማሳሰቢያዎች ተደግፏል።*

***ቁልፍ ግኝት 1፡- MCPS ከMCPS ታሪክ ቁልፍ አጋጣሚዎች የዳበሩና ውስብስብ የፕሮግራሞች ስርአት ለመፍጠር እርስ በእርሳቸው የተደራረቡ እና ርትአዊነትን ጨምሮ ከዲስትሪክቱ ዋነኛ እሴቶች ጋር ሙሉ በሙሉ ያልተስተካከሉ ብዙ የተለያዩ choice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ያቀርባል።*** *ባለፉት 40 አመቶች፣ MCPS በበጎ ፈቃድ የመቀራረብ ጥረቶችና የተማሪዎች ብቸኛ አካዴሚያዊ ፍላጎቶች ላማሟላት—ከጂዮግራፊ አንፃር ስፊ እና የአይነተ-ብዙ/diverse እየጨመረ በሚሄድበት የት/ቤት ዲስትርክት በአሁኑ ወቅት በሀይል እያደገና የት/ቤት ስፋትና በጀቶች ትርጉም ያዘሉ ፈታናዎች በሚፈጥሩበት ሁኔታ—የተለያዩ ፕሮግራሞችን አዳብሯል። የማግኔት ፕሮግራሞች በመጀመርያ የዳበሩት በ1970ዎቹ የትምህርት ቦርድ መመርያ ACD፣ Quality Integrated Education/ጥራት ያለው የተወሀሀደ ትምህርት አካል በመሆን፣ የአይነተ-ብዙነት/diversityን ለመንከባከብና የዘር ልዩነትን ለማስወገድ ነው።*

*የመጀምርያዎቹ ማግኔቶች ወደ ሶስት አይነት ፕሮግራሞች ተሸጋግረዋል—የቋንቋ ዝፍቀት/immersion በኤሌሜንታሪና በመካከለኛ ት/ቤቶች ደረጃ በወላጆች ለልጆቻቸው በሁለተኛ ቋንቋ ያላቸውን ፍላጎት የሚያስተናግድ፣ የኤሌመንታሪ ማእከሎች ከፍተኛ ተሰጥኦ ላላቸው ተማሪዎች፣ እና ለከፍተኛ ተሰጥኦ ለላቸው ተማሪዎች ልዩ አካዴሚያዊ ፍላጎት ላላቸው እንዲስማሙ የተተለሙ በመካከለኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች*

የሚካሄዱ የማግኔትና የትግባሬ ፕሮግራሞች፣ እና ለአካባቢ ኮንሶርሽ። የቋንቋ ዝፍቀት ፕሮግራሞች በሎተሪ/እጣ የተመሰረቱ ናቸው፣ በሌላ በኩል የኤሌሚንታሪ ማእከሎች፣ እንዲሁም በመካከለኛና በሁለተኛ ት/ቤት ደረጃ የሚገኙ የማግኔትና የትግባሬ ፕሮግራሞች፣ ልዩ የምርጫ መስፈርቶች ያላቸው በአካዴሚ ተወዳዳሪ ፕሮግራሞች ናቸው።

ስስቱ የአካባቢ ኮንሶርሽ የዳበሩት በ1998 እና በ2005 መካከል ነው፣ በዲስትሪክቱ ከዳር እስከ ዳር እያደጉ በመጡ ምዝገባዎች እና አዳዲስ ት/ቤቶች መክፈት ሊያስከትል ከሚችለው በት/ቤቶች ውስጥ የዘር መለያየት እምቅ የተፅእኖ ስጋት አንፃር ግብረመልስ በመሆን። Northeast Consortium/ሰሜናዊ-ምስራቅ ኮንሶርሽም (NEC) እና Downcounty Consortium/ዳውንካውንቲ ኮንሶርሽም (DCC) በሁለተኛ ት/ቤት ደረጃ እና የመካከልኛ ደረጃ ት/ቤት Magnet Consortium/ማግኔት ኮንሶርሽም (MSMC) በዲስትሪክት ሴማዊ ፕሮግራሞች አማካይነት ተማሪዎችን ይስባሉ እናም የተማሪዎችን ምርጫዎች፣ ማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ ይዘት፣ እና ሌሎች ዴሞግራፊክ ታሳቢዎችን ግንዛቤ ውስጥ በሚያስገቡ የአቦ-ሰጥ ሎተሪ ይጠቀማሉ።

የተላየ የፕሮግራሞች ቡድን፣ እንደወቅታዊ ይዘታው፣ ከSPF ጋር የተቀነባበረ በሚገባ የተገለፀ ተልእኮ አይጋራም። ስለፕሮግራሞቹ የጋራ ቋንቋ አለመኖር ለተዋሰኑ ወላጆች ወይም የማህበረሰብ አባላት ምን ፕሮግራሞች እንዳሉ እና ለልጃቸው ፕሮግራሞቹ ሊሰጡ የሚችሉት ጥቅም—አንዱ ካንዱ ያለውም ልዩነት—ለመገንዘብ አዳጋች ያደርገዋል። በትኩረት ቡድኖችና ቃለ መጠይቆች፣ የMCPS ወላጆች፣ ተማሪዎች፣ እና ሰራተኞች ከፍተኛ ጥራት እና ልዩ የማስተማር ፕሮግራሞ ለተማሪዎች በማቅረብ ረገድ ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ለማህበረሰቡ ጠቃሚ ሀብቶች መሆናቸውን ተስማምተዋል። የአካዴሚያው ጥንካሬ ደረጃ በልዩ ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ተፈላጊ መሆኑን ጨምረዋል። ቢሆንም፣ በchoice እና በልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ይሳተፉም አይሳተፉም፣ ሁሉም የMCPS ተማሪዎች ለጠንካራ ትምህርት መዳረሻ ማግኘት መቻል አለባቸው ብለዋል። ሁሉም ት/ቤቶች ውጤታማና ጠንካራ አማራጮች፣ የተለያየ አማራጭና የተፋጠነ ትምህርት ለሁሉም ተማሪዎች ማቅረብ አለባቸው በማለት ጨምረው ተናግረዋል። በመጨረሻ፣ የትምህርት ጥራት በተማሪ መኖርያ ቤት ጂዮግርፊካዊ አቀማመጥ አማክይነት መለያየት የለም ብለው ጨምረዋል። እነዚህ የመጨረሻዎቹ ስሜቶች የ2017 በጀት ዘመን በጀት ረቂቅ ሲያቀርብ በSuperintendent Larry Bowers ተንፀባርቀው ነበር፣ እንዳለውም፣ "ተመሪዎቻችን ፍላጎታቸውን ከሚያሟላውና ለልቀት ከሚገፋፋቸው የትምህርት ፕሮግራም እንዳይሳተፉ የከለኳቸውን መዋቅራዊና ስርአታዊ መዝጊያዎችን ፈጥረናል። እነዚህን መዝጊያዎች እና የነዚህ ፕሮግራም ውሳኔዎች በግኝት ክፍተቶቻችን ያስከተሉትን ተፅእኖ ያልታሰቡ ውጤቶች መቋቋም አለብን።

- ***ማሳሰብያ 1፡- የACDን መመርያ መከለስ፣** Quality Integrated Education/ጥራት የተቀነባበረበት ትምህርት፣ ለchoice እና ለልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች የተለየ ተልእኮ ለማጣራት ከማህበረሰብ እና የሰራተኛ ባለ ጉዳዮች ግቦችንና የፕሮግራሞቹ አላማ በጥራት ለመግለፅ የተሰጠ አስታያየት ጋር፣ እንዲሁም ከMCPS ዋነኛ እሴቶች እና MCPS ርትአዊነት እና በሰፊ ደረጃ በሁሉም ት/ቤቶች ለጠንካራ ትምህርት ተፈላጊዎችን እና እድሎችን በሰፊ ደረጃ ከፍ ማድረግ እንዳለበት ያለውን የባልጉዳዮች ጠንካራ እምነት ጋር መሰለፋቸው።*

**ቁልፍ ግኝት 2፡- ስለ የMCPS ሰፋፊ አይነቶች choice እና ለልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች በእኩልነት አይሰራጩም፣ ይህም ለፕሮግራሞቹ የመዳረስ ርትአዊነት ላይ ትፅእኖ እያደረገ ነው።** MCPS ስለ ፕሮግራሞቹ መረጃዎች የወላጆችና ከማህበረሰብ አባላት ጋር ለመጋራት የተለያዩ የመገናኛ መሳርፍያዎችን አዳብሮ ተግባራዊ አድርጓል። እነዚህ የሚያካትቱት ለMCPS ቤተሰቦች በሳብ ት ቋንቋዎች የሚላኩ የታተሙ ቁሳቁሶች፣ በዲስትሪክቱ ድርጣቢያ እና የPTA አውቶማቲክ መልእክት ማሰራጫዎች/listservs ድርገፆች፣ መረጃዊ

ስብሰባዎች በት/ቤቶች በእንግሊዘኛና በስፓኒሽ፤ በፕሮግራም ደረጃ ክፍት አዳራሾች/Open Houses፤ እና በት/ቤት በተመሰረቱ አማካሪዎች፣ ሰራተኞች፣ እና ርእሰመምህራን የውጭ ግንኙነቶች።

እነዚህ ጥረቶች በሞላ እያሉም፣ የፕሮግራም ትግባሬዎችና ከትኩረት ቡድኖች አህዞች እንደሚያመለክቱ ስለነዚህ ፕሮግርሞች መረጃዎች ለተወሰኑ የምህበረሰብ ክፍሎች፣ በተለይም ሂስፓኒክ/ላቲኖ፣ ጥቁር/አፍሪካን አመሪካን፤ እንግሊዘኛ የመይናገሩ፣ እና አነስተኛ ገቢ ቤተሰቦች ለሌሎች ቡድኖች እንደሚደርሷቸው አይደርሳቸውም። በተጨማሪ፣ ከሰራተኞችና ከወላጆች ጋር በተካሄዱ የትኩረት ቡድኖች፣ አንዳንድ መልስ ሰጭዎች የዲስትሪክቱ መልእክቶች ለግንዛቤ የሚያደንግሩና ወልጆች ነፃ ምርምር እንዲያካሂዱየሚጠይቁ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ዲስትሪክቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ከወላጆች ጋር ፊት-ለፊት ለመገናኘት በቂ የውጭ ግንኙነትና የቅጥር ስራ አያካሂድም እናም ከእንግሊዘኛ በስተቀር በሌሎች ቋንቋዎች በቂ መረጃ አያቀርብም ብለው በጭማሪ ተናግረዋል። ስለሆነም፣ የነዚህን አይነት መገናኛዎችና የህዝብ ግንኙነት የሚመርጡ ወይም የሚፈልጉ ቤተሰቦች ሌሎች ቤተሰቦች ያላቸውን ያህል ለመረጃዎች ርትአዊ መዳረሻ የላቸውም።

- **ማሳሰብያ 2:-** በMCPS ውስጥ በሚገባ ውክልና ካላገኙና ለማግኘት አስቸጋሪ ከሆኑቤተሰቦ ጋር ለመገናኘት፣ ግንኙነት ለመፍጠር፣ ለመመልመል እና መረጃ ለመሻረክ አዳዲስ ስልቶችን ማዳበርና መተግበር። እነዚህ ስልቶች፣ በነሱ ሳይወሰኑ፣ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርባቸዋል:-
  - የተቀናጁ መገናኛዎች በቀላሉ ለመገንዘብ በሚቻል ቋንቋ፤
  - ነባር የመገናኛ መሳርያዎች ለባህላዊ ትክክለኛነት/validity መከለስ፤
  - በማህበራዊ ክውነቶችና ቦታዎች ቤተሰቦችን መገናኘት፤
  - በቤተሰቦች ምልመላ ለአንድ-ለአንድ ወይም ለገልሰብ ግንግኙነት እድሎች መጨመር፤ እና
  - ተጨማሪ ቁሳቁሶችና ክውነቶች ኸእንግሊዘኛ ሌላ በሆኑ ቋንቋዎች ማከናወን።

**ቁልፍ ግኝት 3:- ወደ አካዴሚያዊ ምርጥ ፕሮግራሞች በምዝገባና በአቀባበል መጠኖች ጉልህ የሆኑ የዘርና የማህበራው-እጼኮኖሚያዊ ልዩነቶች አሉ፣ ይህም ከሁሉም በስተጀርባ የመዳረሻ መዝግያዎችን ለማስወገድ ተማሪዎችን ለነዚህ ፕሮግራሞች የመምረጫ መስፈርቶችንና ሂደቶችን የመከለስ አስፈላጊነትን ይጠቁማል።** ወደ ኤሌሜንታሪ ማእከሎችና ለሁለተኛ ደረጃ ማግኔትና የትግባሬ ፕሮግራሞች የማመልከቻዎችና የመቀበል አህዞች በነዚህ ፕሮግራሞች ለመምረጥና ለመመዝገብ ከነጮች፣ እስያውያን፣ እና ከከበለ ከፍተኛ ገቢ ተማሪዎች ይልቅ ሂስፓኒክ/ላቲኖ፣ ጥቁር/አፍሪካን አሜሪካን፣ Limited English Proficient/የተወሰነ የእንግሊዘኛ ችሎታ (LEP)፣ ልዩ ትምህርት፣ እና አነስተኛ ገቢ ያለቸው ያነሰ እድል እንዳላቸው ያሳያሉ። ስለሆነም፣ ሂስፓኒክ/ላቲኖ፣ ጥቁር/አፍሪካን አሜሪካን፣ (LEP)፣ ልዩ ትምህርት፣ እና አነስተኛ ገቢ ያለቸው አማሪዎች ከዲስትሪክት-አቀፍ የምዝገባ አህዝ ጋር ሲወዳደር በአካዴሚያዊ ምርጥ ፕሮግራሞች ከሚጠበቀው በታች ተወክለዋል።

ምንም እንኳን MCPS በኤሌሜንታሪ ማእከሎችና በሁለተኛ ደረጃ ማግኔትና ትግባሬ ፕሮግራሞች የሁሉንም ቡድኖች መወከል ቀጠተኛ ጥረቶች ቢያአድግም እነዚህ አህዞች ይገኛሉ። ድስትሪክቱ በምርጫ ሂደት፣ በእውቀት/cognitive ግመማዎች በተጨማሪ፣ የሚከተሉትን በሚያካትቱ በተለያዩ ሂደቶች ይገለገላል፣ የመምህራን ጥቆማዎችና ሌሎች በት/ቤቶች የተመሰረቱ አስተያየቶች፣ የሪፖርት ካርድ ማርኮች፣ ብቸኛ የተማሪ አጭር መግለጫዎች/profiles፤ እንደ ነፃና ቅናሽ ዋጋ ምግቦች (FARMS)፣ እና በአካባቢ/ቤት የማሰብና የመመራመር የእኩያ ቡድን አለማኖር። ቢሆንም፣ የአይነተ-ብዙነት/diversity አለመኖር እና በነዚህ ፕሮግራሞች የተወሰኑ የተማሪ ቡድኖች ከሚጠበቀው በታች መወከል ሂደቱ ከሚገባው በላይ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ጠቋሚዎች ላይ ማተኮር ወይም ተጨማሪ የተማሪ ችሎታ መለኪያዎች ማጎናዘብ ሊያስፈልግ ይችላል። እነዚህ ጠቋሚዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ የባለተሰጥኦን ትርጉም የእውቀት ያል።ሆኑ መለኪያዎች እንደ

ተነሳሽነትና ፅነአት እንዲያካትቱ ማስፋት፣ በቡድን በተለዩ የተማሪን አፈፃፀም ዘዴዎች ተመጣጣኝ የበስተኋላ ካላቸው ከት/ቤት ጓዶቹ/ቿ አንፃር በሚለኩ ዘዴዎች መጠቀም፣ በዲስትሪክቱ ከላኪ የኤሌሜንታሪና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብልጫ 56-10% የሆኑ ተማሪዎችን በኦቶማቲክ ለመቀበል በመጠየቅ/በመፍቀድ፣ ወይም በዘገባው የተመለከቱት በሀገሪቱ በሌሎች ዲስትሪክቶች አገልግሎት ላይ የዋሉ ዘዴዎች። በተጭማሪ፣ እነዚህ አሀዞች እነዚህ ዲስትሪክቶች የቆዩ የMCPS's Young Scholars Program/የወጣት ምሁራን ፕሮግራም ከሚገባው በታች ውክልና ካላቸው የጀማሪ የክፍል ደረጃ ቡድኖች ተማሪዎችን ለ አካዴሚያዊ ምርጥ ፕሮግራሞች መለየትን የመሳሰሉ ተጨማሪ ፕሮግራሞች ወይም ምውሳርያዎች አገልግሎት ላይ ማዋል አለባቸው። እነዚህ ፕሮግራሞች ከሚገባው በታች የተወከሉ ተማሪዎቹ የአመልካች ክምችትን ለመጨመር እና የበለጥ የተሳታፊነት ደረጃ ለማበረታታት ያገለግላሉ።

- ***ማሳሰብያ 3ሀ:- የኤሌሜንታሪ ማእከሎች ለባለከፍተኛ ተሰጥኦ ተማሪዎችና የሁለተኛ ደረጃ የማግኔት ፕሮግራሞች ለሚያካትቱ የMCPS አካዴሚያዊ ተወዳዳሪ ፕሮግራሞች አገልግሎት ለሚውል የመምረጫ ሂደት ማሻሻያዎች መተግበር፣ እነዚህን ፕሮግራሞች በፕሮግራሙ ለመበልፀግ ችሎታ እንዳለቸ ከሚያሳዩት መካከል በርትአዊነት መምረጥ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ፣ የእውቀት ባልሆኑ/non-cognitive መስፈርቶች መጠቀምን የሚያካትቱ፣ በቡድን በተለዩ የተማሪን አፈፃፀም ዘዴዎች ተመጣጣኝ የበስተኋላ ካላቸው ከት/ቤት ጓዶቹ/ቿ አንፃር በሚለኩ ዘዴዎች መጠቀም፣ እና ወይም በዲስትሪክቱ ከላኪ የኤሌሜንታሪና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብልጫ 56-10% የሆኑ ተማሪዎችን በኦቶማቲክ ለመቀበል የሚጠይቅ ሂደት።***

- ***ማሳሰብያ 3ለ:- የMCPS ተማሪ ህዝብ ሰፊ ክፍል በ አካዴሚያዊ ምርጥ ፕሮግራሞች ተሰትፎ ለመደገፍ የልጅነት ጊዜ ተሰጥኦ ማዳበርያ ፕሮግራሞች ለአነስተኛ ውክልና ላላቸው ቡድኖች ልጆች ለማስፋፋትና ለማበልፀግ በመገልገያዎች ሙአለንዋይ ፈሰስ ማድረግ።***

***ቁልፍ ግኝት 4:- የዲስትሪክቱ ትግባሬ በተወሰኑ የወቅታዊው ቦርድ መመርያ JEE፣ Student Transfers/የተማሪ ዝውውር ደንቦች፣ ከMCPS ለchoice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ርትአዊ መዳረሻ ለማቅረብ ካለው ግብ ጋር ሙሉ ብሙሉ አልተቀነባበረም።*** በተለይም፣ የቦርዱ ወቅታዊ መመርያ ርትአዊ መዳረሻ ሙሉ በሙሉ በማይደግፉበት መንገዶች የተተገበሩ ሁለት ደንቦችን ያካትታል፣- 1) በአሁኑ ወቅት ተማሪዎች የኤሌሜንታሪ የቋንቋ ዝፍቀት ፕሮግራም የሚ(ምት)ከታትል ታላቅ ወንድም/እህት ካላቸው ወደ ፕሮግራሙ በአውቶማቲክ የመግባት ፈቃድ ያገኛሉ፤ እና 2) አንድ የተወሰነ መካከለኛ ት/ቤት የሚከታተሉ ተማሪዎች በዚያው ት/ቤት መጋቢ ቅርፀት/feeder pattern ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ የፕሮግራም ምክንያቶች ተገቢ ትኩረት ሳይሰጣቸው፣ መቀጠል ይችላሉ።

መጀመርያ፣ በኤሌሜንታሪ የቋንቋ ዝፍቀት ፕሮግራሞች የወንድም/እህት አገናኝ ትግባሬ አሀዞች በ2013-14 ሎተሪ ውስጥ ወደ ፕሮግራሞቹ የመገባት ፈቃድ ያገኙ ተማሪዎች ውስጥ ሲሶ አካባቢዎቹ (29.8%) ወንድም/እህቶች እንደነበሩ ያሳያሉ። ለተወሰኑ ፕሮግራሞች ምዝነቱ/proportion እስከ 45.8% ድረስ ከፍ ብሎ ነበር። ይህ የውንድም/እህት አገናኝ ወንድም/እህት ላልሆኑ የመዳረሻ ርትአዊነትን ያደናቅፋል ምክንያቱም ሊኖሩ የሚችሉ ቦታዎችን ጠቅላላ ቁጥር ይቀንሳል።

ሁለተኛ፣ በመመርያ JEE ከመካከለኛ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አውቶማቲክ ሽግግር ደንብ አባባል/articulation ርትአዊ መዳረሻን ያከብደዋል ምክንያቱም በት/ቤት መጠን ተፅእኖ ያደርጋል ይህም፣ በፕሮግራም ምክንያት በሚያስደስት የስራ አቅጣጫ/career pathway መከታተል ወይም ከመጋቢ ቅርፀት/feeder pattern ውጭ በሴማዊ ትኩረት ጥናት መቀጠል በመሳሰሉት ዝውውር የሚፈልጉ ተማሪዎችን ቦታ ሊያጣብብ ስለሚችል።

የሚከተሉት ማሳሰብያዎች መገናዘብ ያለባቸው ለመመርያ JEE፣ *Student Transfers/የተማሪ ዝውውሮች*፣ ለውጦች ማድረግ፣ ለተማሪ ዝውውር ጥያቄዎች (COSAs) የግምገማና የማፅደቅ ሂደት ማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ ይዘት በግልፅ እንደ ታሳቢ ሆኖ ካልተቀመጠ በት/ቤቶች ውስጥ የበለጠ ማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ መገለልን ሊያስከትል እንደሚችል ከሚለው አውደ ንባብ አንፃር ነው።

- ማሳሰብያ 4ሀ:- የመመርያ JEE *Student Transfers/የተማሪ ዝውውሮች*ክለሳ ማገናዘብ፣ የወንድም/እህት አገናኝ ለቅዝፈት እና ለሌሎች የchoice ፕሮግራሞች አውቶማቲክ አለመሆኑን ለማብራራት፤ በቂ ቦታዎች እስካሉ ድረስ የአመልካቾች ወንድም/እህቶች ልይ የአካዴሚያዊ ፕሮግራም ባለበት የንኑ ት/ቤት መከታተል የሚችሉ ቢሆንም፣ እነዚያ ወንድም/እህቶች፣ በፕሮግራሙ ቦታ እንዲያገኙ፣ እንደ ሎተሪ ለዝፍቀት ፕሮግራሞች በመሳሰሉት የማመልከቻ ሂደቶች እንዲሳታአፉ መጠየቅ አለባቸው።

- ማሳሰብያ 4ለ:- ዲስትሪክቱ የመመርያ JEE፣ *Student Transfers/የተማሪ ዝውውሮችን* ክለሳ፣ የአውቶማቲክ አንቀፅን ከመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በዚያ ይመጋቢ ቅርፀት ክላስተር ውስጥ እስካገናዘበ ድረስ *ወይም* ለፕሮግራም-ነክ ጥያቄዎች ማፅደቅ ማገናዘብ ላይ፣ MCPS የት/ቤትን አቅም እና አይነተ-ብዙነት/diversity ለማራመድና በዜጋ ማግለልን ለማስወገድ የሚያደርገውን ጥረት በሁለቱም ላይ የሚኖረውን ተፅእኖ መተንተን አለበት።

**ቁልፍ ግኝት 5:- የልይ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች በአካባቢ ት/ቤቶች መመደብ የነዚያ ት/ቤቶች የተማሪ ህዝቦች አይነት-ብዙነት/diversity ጨምሮታል፤ ነገር ግን፣ የፕሮግራም ተሳታፊዎችንና የማይሳተፉትን የማወሀጃ መሳርያዎች አለመኖር፣ በት/ቤት-ውስጥ የልዩነት ሁኔታዎችን ፈጥሯል።** በት/ቤቶች ፕሮግራሞችን የመመደብ የመጀመርያ ግብ በነዚያ ት/ቤቶች የአጠቃላይ የተማሪ ህዝቦች አይነተ-ብዙነት/diversity ለመጨማር ከሚለው በሚስማማ ሁኔታ፣ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የተማሪዎች ዴሞግራፊ ፕሮግርሞቹን ከሚያስተናግዱ ት/ቤቶች የተማሪ ህዝቦች በአመርቂ ሁኔታ ልዩ መሆናቸውን የምዝገባ አሀዞች ያሳያሉ። እንዳውም በዝርዝር ሲታይ፣ የቋንቋ ዝቅፈት የኤሌሜንታሪ ማእከሎች፣ እና የሁለተኛ ደረጃ ማግኔት እና የትግባሬ ፕሮግራሞች ከምርጫ አቀባበል መስፈርቶች ጋር የነጭ፣ እስያዊ እና ባለ ከፍተኛ ገቢ ተማሪዎች ፕሮግራሙን ከሚያስተናግዱ ት/ቤቶች በከፍተኛ ሚዛኖች ይመዘገባሉ፣ እና አነስተኛ ሚዛኖች ደሞ ለሂስፓኒክ/ላቲኖ፣ ጥቁር/አፍሪካን አሜሪካን፣ LEP፣ እና አነስተኛ ገቢ ተማሪዎች። በተጨማሪ፣ ፕሮግራሞቹ የተተለሙት ተመሪዎችን በተለያዩ ክፍሎች ለመምደብ ቢያንስ በቀኑ ለተወአነ ጊዜ ሉ ስርአተትምህርትና የማስተማር ሴማ ማቅረብ እንዳስፈላጊነቱ። ይህ በጣም ልዩነት ባላቸው የተማሪ ህዝቦች እና ልዩ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች መገለል መገጣጠም የት/ቤት-ውስጥ ልዩነት ልዩ ፕሮግራሞች በሚያስተናግዱ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች፣ ወላጆች እና ሰራተኞች አስተያየቶችን አፍልቋል።

- ማሳሰብያ 5:- የፕሮግራም ተሳታፊዎችና የአካባቢ ት/ቤት ተማሪዎች ትርጉም ያላቸው ማህበራዊና አካዴሚያዊ ግንኙነቶች እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ ፕሮግራሞቹን በሚያስተናግዱ ት/ቤቶች ውስጥ ይበልጥ ለተሟላ የልዩ ፕሮግራሞች የመወሀሀድ ስልቶች ለመፍጠር ሂደት ማቅለል፣ እንደ የልዩዎች/specials ወይም ምርጫዎች/electives ሰፊ አጠቃቀም፣ የጋራ ምሳ ወይም የእረፍት ክፍለ ጊዜዎች፣ እና ከትምህርት ውጭ ፕሮግራሞች እንዳላቸው ማረጋገጥ።

**ቁልፍ ግኝት 6:- የዘር፣ የትውልድ፣ እና የማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ አይነት-ብዙነት/diversity በመራመድ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮንሶርሽ (DCC እና NEC) ይልቅ MSMC ይበልጥ ስኬታማ ነበር በአብዛኛው በዴሚግርፊ መሸጋሸግ እንዲሁም በሶስት ፕሮግራማዊ ንጥረነገሮች ምክንያት:- MSMC፣ ከDCC እና ከNEC አንፃር፣ በመሰረታዊ መስኮች አይጠቀምም፣ ከክልል-ውጭ ተመሪዎችን ይቀበላል፣ ግልጽ የሆኑ ሞሉ-ት/ቢት ሴማዎች አዳብሮ ተግባራዊ አድርጓል።** የሶስቱ ኮንሶርሽዎች የምዝገባ አሀዞች ዘር፣ ትውልድ፣ እና ማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ ይዘትን በሚመለከት ከሁለቱ ኮንሶርሽዎች ይልቅ MSMC

አይነተ-ብዙ የተማሪ ህዝቦችን በመሳብ ይበልጥ ስኬታማ እንደሆነ ያሳያሉ። ከኮንሶርሽም-ውጭ የሆኑ ተመሪዎችን መቀበል ለMSMC ስኬት ቁልፍ ክፍለ አካል መሆኑን አህዞቹ በተጨማሪ ያሳያሉ፣ እናም ከኮንሶርሽም-ውጭ የሆኑ ተምሪዎች ወደ ት/ቤቶቹ የሚሳቡ ባብዛኛው በማግኔት ሰማዎችና ፕሮግራሞች ምክንያት ነው።

አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የመጀመርያውን የምርጫ ት/ቤት የሚያገኙት በchoice ሂደት መሆኑን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮንሶርሻ አህዞች ያሳያሉ (89% በNEC እና 75% በDCC)፣ አብዛኛዎቹም በchoice ሂደት ባጠቃላይ ተደስተዋል። አህዞች በተጨማሪ የሚያሳዩት የተማሪዎች በግምት ግማሾቹ NEC (50%) እና DCC (42%) የመሰረታዊ መስካቸውን ት/ቤት እንደሚመርጡ ነው፣ ይህም በአይነተ-ብዙነት/diversity ለመጨመር የchoice ሂደት ተፅእኖ ቀንሶታል ማለት ነው። በሰረታዊ መስኮች የክትትል ቀጠናዎች አይደሉም፤ ይልቁንስ፣ በያንዳንዱ ት/ቤት አጠገብ ወይ ዙርያ የተበታተኑ/non-contiguous ናቸው፣ የተመሰረቱትም ተማሪዎችን ቤታቸው አጠገብ የመረጡትን ለመከታተል ለማስቻልብሌላ በኩል ደግሞ፣ ቢያንስ መጀመርያ በዳበሩበት ወቅት፣ የዘር መወሀሀድን ለማራመድ ነበር።

በትኩረት ቡድኖች ውስጥ፣ የተወሰኑ ተማሪዎችና ወላጆች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮንሶርሻ ሴማዎች ብዛት ያላቸው ተማሪዎችን ከመሰረታዊ መስክ ውጭ ለመሳብ ብቃት ያለው ጉልህነት የላቸውም በማለት ቅሬታቸውን ገልፀዋል። በተጨማሪ፣ በኮንሶርሻ አገልግሎት የሚያገኙ የካውንቲ መስኮች ከዳር እስከ ዳር በሚካሄደው የዴሞግራፊ ሽግሽግ ምክንያት በሶስቱም ኮንሶርሻ የሚገኙ የተማሪ ህዝቦች በአይነተ-ብዙነት/diversity ዝቅ ብለዋል። ስለሆነም፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮንሶርሻ ከክልል-ውጭ ተማሪዎች ስለማይቀበሉና በመለያ/signature ሴማዎቻቸው የጥንካሬ መቀያየር ስላለ፣ በተሳታፊ ት/ቤቶች አይነተ-ብዙነት/diversityን በማራመድ ያነሰ ስኬት አሳይተዋል።
በተጨማሪ፣ የMCPS ሁለተኛ ደረጃ ክንሶርሻ በአነስተኛ የትምህርት ማህበረሰቦች (SLC) ውጤታማነት ተማሪዎችን ለመሳብ ችለዋል። የሆነ ሆኖ፣ የSLCን ሞዴል ለመተግባር በካውንቲው ከዳር እስከ ዳር የሚገኙ የት/ቤት ዲስትሪክቶች ፈተናዎች እንደገጠሟቸው አካዴሚያዊ ምርምር አሳይቷል። በሱ ፈንታ፣ የተወሰኑ ዲስትሪክቶች፣ ለምሳሌ Jefferson County Public Schoolsን ጨምሮ፣ ወደ ይበልጥ ውጤታማ ወደ ሆነው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት choice ስራ መንገዶች/career pathways በጠንካራ የኮሌጅና በስራ-ትኩረት መንገዶች ለሚጠቀሙ ተማሪዎች ምርጫዎች ወደሚሰጠው እና አይነተ-ብዙነት/diversity ወደሚያረምደው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

- ➢ **ማሳሰብያ 6ሀ፡-** በያንዳንዱ የDCC እና የNEC ት/ቤት የሚሰጡ የፊርማ/signature እና የአካዴሚ ሴማዎች ከዲስትሪክቱ SPF ጋር የሚስማሙ አማራጭ መስጠታቸውን እና፣ የስራ ትምህርት መንገዶችን የመሰሉ፣ አለዚያ በአካባቢ ት/ቤቶች ለማይሰጡ ፕሮግራሞች መዳረሻ ማቅረባቸውን ለማረጋገጥ ሁለገብ ግምገማ ማካሄድ።

- ➢ **ማሳሰብያ 6ለ፡-** የመሰረታዊ መስኮች አጠቃቀምን እና ለኮንሶርሽም-ውጭ ተማሪዎች በመለያ/signature ፕሮግራሞችና ሴማዎች ለመመዝገብ የመቀመጫ ቁጥር ለመወሰን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮንሶርሽም ሞዴልን የመከለስ ጥቅምና ጉዳት እና ተፅእኖ መገምገም።

**ቁልፍ ግኝት 7፡- የchoice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች አጠቃላይ ፍላጎት በMCPS ለፕሮግራሞቹ ከተደረገው የመቀመጫዎች/ቦታዎች አቅርቦት በላይ ነው።** በ2013–14፣ 14.5% የMCPS ተማሪዎች በchoice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ተመዘገቡ። የሆነ ሆኖ፣ ብዙ ተማሪዎች በቦታዎች አቅርቦት እጥረት ምክንያት ፕሮግራሞቹ ጋ መድረስ አይችሉም። ለኤሌሜንታሪ ቋንቋ ዝፍቀት፣ በየአመቱ የሁሉም አመልካቾች በግምት

ግማሾቹ መጠባበቂያ ላይ ይቀመጣሉ። በተጨማሪ፣ ለኤሌሜንታሪ ማእከሎች ለከፍተኛ ተሰጥኦ ካመለከቱት 18%፣ ለመካከለኛ ት/ቤት ማግኔቶች ካመለከቱት 26%፣ እና ለሁለተኛ ደረጃ ማግኔቶችና ለትግባሬ ፕሮግራሞች ካመለከቱት 37% ብቻ ለመመዝገብ ተጋብዘዋል።

የመቀመጫዎች/ቦታዎች አቅርቦት እጥረት በዲስትሪክቱ ከዳር እስከዳር በምዝገባ እድገት ተባብሷል። የዲስትሪክት ምዝገባ አዝማምያ አሀኣዞች በMCPS የሚመዘገቡ የተማሪዎች ቁጥር ከ2008 ጀምሮ በየአመቱ በአማካይ ከ2,000 ተማሪዎች በላይ መጨመሩን ያሳያሉ። ያም ሆኖ፣ የመጨረሻው የወንበሮች/ቦታዎች ቁጥር የመጣው በግምት ከአስራአማስት ኣመት በፊት በCollege Gardens ES የቻይኒዝ ዝፍቀት ፕሮግራም፣ በChevy Chase ES የኤሌሜንታሪ ማእከል፣ እና በRoberto Clemente MS እና በPoolesville HS የማግኔት ፕሮግራሞች መፈጠር ጋር ነው።

በማህበረሰብ የዳሰሳ ጥናት በትኩረት ቡድኖች አመካይነት የተሰበሰቡ የአይነት አሀዞች በተጨማሪ ያሳዩት ለልዩ ፕሮግራሞች ከፍተኛ ፍላጎት እና በMCPS ውስጥ ለchoice እና ለልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ተጨማሪ እድሎች ከወላጆች፣ ሰራተኞኣ፣ እና ተማሪዎች የጋራ ጥያቄ መኖሩን ነው። የሆነ ሆኖ፣ ማንኛውም መስፋፋት የእነዚህን ፕሮግራሞች ርትአዊ መዳረሻን እና እላይ የተጠቀሱት ሌሎች ፈተናዎችን ለመመልከት ከሚደረጉ ጥረቶች ጋር አብሮ መተሳሰር ይኖርበታል የሚል ቅሬታ ባለጉዳዮች በተጨማሪ ገልፀዋል፣ እንዲሁም MCPS ለጠንካራ ትምህርት በሁሉም ት/ቤቶች ተጠባቂዎችንና እድሎችን ከፍ በማድረግ ርትአዊነትን በሰፊ ደረጃ እንዲከታተል አስፈላጊነት የባለጉዳዮች ጠንካራ እምነት መሆኑም።

ከሰራተኛና የትራንስፖርት ዋጋዎች ትንተና የተገኙ አሀዞች የወንበሮች/ቦታዎች መስፋፋት በፕሮግራም በጀቶች ጭማሪ ማድረግ የግድ እንዳልሆነ ይጠቁማሉ፤ ቢሆንም ለሰራተኛ (ለፕሮግራሞቹ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ለመመልመልና ለመቅጠር)፣ እንዲሁም የት/ቤት መጠን ፈተናዎች ሊያቀርብ ይችላል። በተጨማሪ፣ choice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ለመከታተል የሚጨመሩትን የተማሪዎችን ቁጥር ለማስተናገድ የትራንስፖርት መስፋፋት ከዲስትሪክቱ ተጨማሪ ሙአለንዋይሆች ይጠይቃል።

ምርምርና መለኪያ MCPS ውስጥ በአሁኑ ወቅት በመተግበር ላይ ያሉ የፕሮግራም ሞዴሎች ላይ በርካታ choice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራም ሞዴሎች መገንባት ላይ እንዳሉ ይጠቁማል ነገር ግን ከዲስትሪክቱ SPF ይበልጥ መቀነባበር ሊሰጥ ይችላል። ለምሳሌ፣ በየቋንቋ ዝፍቀት መስክ፣ አካዴሚያዊ ምርምር የሁለት ቋንቋ ዝፍቀት—እንግሊዘኛ ተናጋሪዎችንና የሌሎች ቋንቋዎች የትውልድ ተናጋሪዎችን የሚያገለግሉ ፕሮግራሞች—የመዳረሻ ርትአዊነትንና የተማሪ አካዴሚያዊ ውጤቶችን በመጨመር አወንታዊ ጥቅሞች አሳይቷል። በተጨማሪ፣ ማግኔት ፕሮግራሞች ላይ የተካሄደ ምርምር የሙሉ-ት/ቤት ሞዴሎች ጥቅሞችን፣ እንዲሁም የአካዴሚያዊ-አማራጭ/academically-selective እና አማራጭ-ቢስ/non-selective ፕሮግራሞች አጠቃቀም ለሰፊ የተማሪዎች ክፍል ማቅረብን ይጠቁማል።

- ማሳሰብያ 7:- ከዲስትሪክት ምዝገባና ፍላጎት እድገት ጋር አብሮ ለመራመድ በchoice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ውስጥ የወንበር/ቦታ መጠን ለማስፋት MCPS የሙአለንዋይ ፈሰሰ እስካደረገ ድረስ፣ እነዚህ ጥረቶች ከዲስትሪክቱ ዋነኛ እሴቶች ጋር፣ ርትአዊነትን ጨምሮ፣ የተቀነባበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፣ እና ሁለትዮሽ ቋንቋ እና ሙሉ-ት/ቤት፣ በሴማ-የተመሰረቱ በሎተሪ የተመሰረቱ የማግኔት ፕሮግራሞች የመቀብል ሂደቶች በተቀዳሚ በተማሪ ፍላጎት የሚተማመኑ ሂደቶችን የመሳሰሉ ሰፋ ያሉ የተለያዩ ሞዴሎች ማገናዘብ አለበት።

**ቁልፍ ግኝት 8፡- MCPS በchoice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ተስትፎንና ለቆ መሄድን በስነስርአት አይከታተልም።** የዲስትሪክቱ የአሀዝ ስርአቶች የተማሪን ምዝገባ በነዚህ ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም የነሱን ሰርጠ ብረት/trajectory በፕሮግራሞች ባሻገር በMCPS ሂደታቸው ዘመን ለመወሰን የፕሮግራም መለያዎች/flags የማስቀመጥ ችሎታ የሚያካትቱ ቢሆንም፣ የፕሮግራም መለያዎች ስነስርአታዊና ዘላቂ አጠቃቀም አለመኖር በchoice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች የሚመዘገቡ ተማሪዎችን ጠባዮችና አፈፃፀም ለመፈተን እና የፕሮግራም ፍፃሜ ወይም መዳከም ለመከታተል የዲስትሪክቱን አቅም ያደናቅፋል። በተጨማሪ፣ ዲስትሪክቱ ፕሮግራሞቹ፣ በተናጠል ወይም ባጠቃላይ፣ የታሰቡትን ግቦች እስከ ምን ድረስ እየመቱ እንደሆነ ቀጣይ ወይም ስነስርአታዊ ግምገማዎች ለማካሄድ ችሎታ የለውም።

- **ማሳሰብያ 8፡-** choice እና ልዩ አካዴሚያዊ ፕሮግራሞች የሚመዘገቡ ተማሪዎችን ለመለየት የፕሮግራሞችን ትግባሬና ተፅእኖ ለመቆጣጠር ተሳትፎን፣ መዳከምን፣ እና አካዴሚያዊና ሌሎች በፕሮግራሙ የሚገኙ የተማሪ ውጤቶችን ለመገምገም በዲስትሪክቱ የአሀዝ ስርአት ውስጥ በሚገኙ ተለዋዋጮች በዘለቄታ መጠቀም።